# መጽሐፈ አክሲማሮስ

## ዘሰድስቱ ዕለታት



አዘጋጅና አሳታሚ፡-
አባ ሠናይ ምስክር
ባሕር ዳር

፲፱፻፺፱ ዓ.ም ታተመ

www.ethiopianorthodox.org

# ሰጋም ሰበለ ሐሑጽሙ

## ቶ·ሊለሰ ቀሰኋሰዘ

©

ያለአዘጋጁና አሳታሚው ፈቃድ መልሶ ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው፡፡



ለእግዚአብሔር ምድር በምልአ፡፡ ዓለምኒ ወኵሉ እለ ይነብሩ ውስቴታ፡፡ ወውእቱ በባህር ሣረራ፡፡ ወበዓፍላግኒ ውእቱ አጽንዓ፡፡ ምድርና መላዋ ለእግዚአብሔር ናት፡፡ ዓለምም በእርስዋም የሚኖሩ ሁሉ፡፡ እርሱ በባሕሮች መሥርቷታልና፡፡ በፈሳሾችም አጽንቷታልና፡፡

መዝ 23፡1-3

www.ethiopianorthodox.org





መታሰቢያነቱ
የባሕር ዳር ፈለገ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳምን ለአርባ
ዓመታት ሲያስተዳድሩ ለቆዩና አሁንም በማስተዳደር
ላይ ላሉት ታላቅ መንፈሳዊ አባት ለመልአከ ገነት
ኃይለ ማርያም ፈንታሁን
ይሁንልኝ::

www.ethiopianorthodox.org

## ምስጋና

ይህን አክሲማርስ መጽሐፍ ለሕትመት እንዲበቃ

- ባላቸው ትርፍ ጊዜ ተጀምሮ እስኪፈጸም ድረስ ከጎኔ ሳይለ[illegible] በኮምፒውተር ጽሑፍና ለቀማ፣ በማቀነባበርም ለረዱ[illegible] ለተከለ መድኅን ከነቤተሰቦቻቸው፤
- በገንዘባቸው ለረዱኝ ለአቶ ተስፋዬ መንግሥት (ወልደ ትንሳኤ)ና ለባለቤታቸው ወ/ሮ ሐረጎ ወንዱ (ወለተ ኪዳን)፣ ለMr. Jhon (ተ/ዮሐንስ)ና ለባለቤታቸው ለወ/ሮ ትዕግስት ይሂነው (ወለተ ሐና)፣ ለMr. Arto(ሀ/ሥላሴ)ና ለባለቤታቸው ለወ/ሮ አስቴር ትዕዛዙ(ዓፀደ ማርያም)፣ ለአቶ ሀብታሙ ብዙነህ (ሀ/ማርያም)ና ለባለቤታቸው ለወ/ሮ የኔወርቅ ታያቸው (ዓፀደ ማርያም) ከነቤተሰቦቻቸው፤
- ሀሳብ ሞራል እና የተለያየ ድጋፍ በመስጠት ላበረታቱኝ፤

የእመቤታችን የቃል ኪዳን ልጆች ሁሉ፤ ሁሉን ማድረግ የማይሳነው እግዚአብሔር የማቱሳላ እድሜን ሰጥቶ፣ በሕይወት ጠብቆ፣ ሥራቸውን አቃንቶ ገንዘባቸውን ባርኮ ያቆይልኝ ዘንድ እየጸለይሁ በእግዚአብሔር ስም ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::




አዘጋጅና አሳታሚ:-

አባ ሥናይ ምስክር

የባሕር ዳር ፈለገ ግዮን ትዱስ ጊዮርጊስ

ገዳም ሰብከተ ወንጌል ኃላፊ

ስልክ- 058 2200849

» 2204565

<u>ባሕር ዳር</u>


www.ethiopianorthodox.org

# ማውጫ


ገጽ

መቅድም ........................ ፩
ታሪክ ........................ ፭

አክሲማርስ ዘእሑድ
- ክፍል አንድ ........................ ፱
- ክፍል ሁለት ........................ ፲፮
- ክፍል ሦስት ........................ ፴፮
- ክፍል አራት ........................ ፵፮

አክሲማርስ ዘሰኑይ
- ክፍል አንድ ........................ ፶፭
- ክፍል ሁለት ........................ ፷፭

አክሲማርስ ዘሠሉስ
- ክፍል አንድ ........................ ፸፫
- ክፍል ሁለት ........................ ፺፱

አክሲማርስ ዘረቡዕ
- ክፍል አንድ ........................ ፻
- ክፍል ሁለት ........................ ፻፳፩

አክሲማርስ ዘሐሙስ
- ክፍል አንድ ........................ ፻፴፰
- ክፍል ሁለት ........................ ፻፵፩

አክሲማርስ ዘዓርብ
- ክፍል አንድ ........................ ፻፵፮
- ክፍል ሁለት ........................ ፻፶፭
- ክፍል ሦስት ........................ ፻፷፱
- ክፍል አራት ........................ ፻፸፩
- ክፍል አምስት ........................ ፻፹፭
- ክፍል ስድስት ........................ ፻፺፫
- ክፍል ሰባት ........................ ፪፻፱
- ክፍል ስምንት ........................ ፪፻፲፱


www.ethiopianorthodox.org

## መግቢያ

**ይህን አክሲማሮስ መጽሐፍ እንዳዘጋጅና እንዳሳትም ያነሳሳኝ ምክንያት**

- የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ብዙ ጊዜ በዋቢነት ይጠቅሱታል:: ነገር ግን እንደተፈላጊነቱ መጠን ተዘጋጅቶና ታትሞ ሕዝበ ክርስቲያኑ ሊጠቀምበት ባለመቻሉ፤
- ሁለተኛውም ከሌሎች መጻሕፍት በመጀመሪያ መታወቅ ያለበት የሥነ ፍጥረት መጽሐፍ መሆኑን በማመን ነው::

ከአሁን በፊት ብዙ ነቢያት በተለያየ መልኩ ቢጽፉም አክሲማሮስ የሚል ስም ሰጥቶ የጎደለውን አምልቶ የረቀቀውን አጉልቶ ሀያ ሁለት ሥነ ፍጥረት ብሎ ቆጥሮ የጻፈ ግን ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ነው::

ስለዚህ ይህንን መጽሐፈ አክሲማሮስ ቀለል ባለ መልኩ ተዘጋጅቶና ታትሞ ሕዝበ ክርስቲያኑ እንዲጠቀምበት በነበረኝ ከፍተኛ ፍላጎት «ሰአሉ ወይትወሀበክሙ ኅሡ ወትረክቡ ጐድጕዱ ወይትረኀወክሙ እስመ ኵሉ ዘይስእል ይነሥእ ወዘሂ የኀሥሥ ይረክብ ወለዘሂ ጐድጕደ ይትረኀዎ:: ማቴ ፯+፯-፱

ለምኑ ይሰጣችኋል ፈልጉ ታገኛላችሁ መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችኋል የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና የሚፈልግም ያገኛል መዝጊያንም የሚያንኳኳ ይከፈትለታል:: ማቴ 7+7-9:: ብሎ ጌታችን እንዳስተማረን እኔም

- በአንዳንድ ገጻማትና አድባራት እንዲሁም ከአባቶች መጽሐፉን በማፈላለግና የተሻለውንም በመምረጥ፤ አንዱ የተወውን ሌላው ያስተካክላል፤ ይህንን ሁሉ በማቀነባበር፤
- አግርኛው እየቀደመ ግእዙ ይከተል የነበረውን በማስተካከልና ሥርዓት በማስያዝ፤ ግእዙ ተጠቅሶ ሳይተረጉም የታለፈውን በመተርጐምና ምዕራፍና ቁጥሩን በመጥቀስ፤

www.ethiopianorthodox.org

# አክሲማሮስ ዘእሑድ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ
ንቀድም በረድኤተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘቦቱ
መድኃኒትነ ጽሒፈ መጽሐፈ አክሲማሮስ ዘቅዱስ
ኤጲፋንዮስ ኤጲስቆጶስ ዘደሴተ ቆጵሮስ ጸሎቱ ወበረከቱ
የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አንድ አምላክ በሚሆን
ድኅነት ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ
አጋዥነት የቆጵሮስ ኤጲስቆጶስ የቅዱስ ኤጲፋንዮስ
አክሲማሮስ መጽሐፍን መጽሐፍ እንጀምራለን፡
ጸሎቱና በረከቱ ከእኛ ጋር ይኑር ለዘላለሙ አሜን።

❖

ቅዳሜ ለእሑድ አጥቢያ በጊዜ ሠርክ ሰባት ፍጥረታትን ፈጠረ። ምንና ምን ቢሉ አራቱ ባሕርያትን፣ ሰማያትን፣ መላእክትን፣ ጨለማን ፈጠረ፤ በባሕርዬ አራት ነገሮች አሉብኝ ሲል አራቱን ባሕርያት ፈጠረ፤ በባሕርዩስ ያሉ አራቱ ባሕርያት ምንና ምን ናቸው ቢሉ

ኃያልነት፣ መንጽሒነት/የሚያነፃ/፣
ፈታሒነት/ፈራጅ/፣ ባዕልነት/ባለጸጋነት/ ናቸው።

www.ethiopianorthodox.org

እሑድ ማለት ለፍጥረት አንደኛ ለቀመር ስድስተኛ ለፀሐይ አምስተኛ ማለት ነው። የአሥራ ሁለቱ ሰዓተ ሌሊት የአሥራ ሁለቱ ሰዓተ መዓልት የሀያ አራቱ ጊዜያት ስምንት ፍጥረት ይህ ነው። ይህስ የተፈጸመው በምን ቀን ነው ቢባል መጋቢት ሀያ ዘጠኝ ቀን ነው።

## አክሲማርስ ዘሰኑይ

፩. ወይቤ እግዚአብሔር ልይኩን ጠፈር ማዕከለ ማይ ከመ ይፍልጥ ማዕከለ ማይ ወማይ ወኮነ ከማሁ ዘፍ ፩፥፮-፱

እግዚአብሔር በሁለተኛው ቀን ምን ፍጥረት ፈጠረ ያሉ እንደሆን እሑድ በጊዜ ሠርክ ለሰኞ አጥቢያ ያች ብዝ ተባዝ ያሳት ውኃ ከምድር ጀምራ እስከ ብሩህ ሰማይ ድረስ መልታ ሰፍታ አድራ ውላ ነበር።

፪. ለይኩን ጠፈር በማዕከለ ሰማይ ብሎ ቢያዝዝ ውኃው ከአራት ተከፈለ። እግዚአብሔርም በውኆች መካከል ጠፈር ይሁን፣ በውኃና ውኃ መካከልም ይከፈል አለ። ዘፍ 1፥6-9 እግዚአብሔርም ጠፈርን አደረገ ከጠፈር በታችና ከጠፈር በላይ ያሉትንም ውኆች ለየ እንዲሁም ሆነ፡ እግዚአብሔር ጠፈርን ሰማይ ብሎ ጠራው። ዘፍ 1፥6-9

፫. ወእምዝ ነሥአ እግዚአብሔር ከፍሳ ለይእቲ ዓባይ ማይ ወአዕረጋ መልዕልተ ሰማየ ማይ ወመልዓት እምጽንፍ እስከ ጽንፍ ወከዊና ፩ደ ቆመት ወጸንዓት ወረግዓት ከመ ሐዊን ወከመ ሰይፍ ዘሀሉ ውስተ ቀቀቡ።

በማዕከል ያለው ሲሦው ውኃ እንደ ቤተ ንጉሥ አዳራሽ ጠፈር ሆና ተመሠረተች ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን

www.ethiopianorthodox.org

፳፩.መኑ ዘደመሮ ለብርሃን ምስለ ጽልመት ወለጽድቅኒ ምስለ ኃጢአት። ፪ቆሮ ፮፥፲፬-፲፭

ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ሕብረት አለው። 2ቆሮ 6፥14-15

እሑድ ማለት አንድ ማለት ነው፤ ሰኑይ ማለት ሁለት ማለት ነው፤ ሰኞ ለፍጥረት ሁለተኛ ለቀመር ሰባተኛ ለፀሐይ ስድስተኛ ማለት ነው። ሁለት ዕለት ዘጠኝ ፍጥረት ይህ ነው። ይህስ የተፈጸመው በምን ቀን ነው ቢባል መጋቢት ሠላሳ ቀን ነው።

# አክሲማሮስ ዘሠሉስ

፩. ወይቤ እግዚአብሔር ለታብቊል ምድር ሐመልማለ ዘርእ ዘይዘራእ በበዘርኡ ወበበዘመዱ ዘፍ ፩፥፲፩-፲፫

እግዚአብሔር ሰኞ ማታ ለማክሰኞ አጥቢያ በጊዜ ሠርክ፣ በዕለተ ሠሉስ ምንና ምን ፍጥረት ፈጠረ ቢሉ፤ ሦስት ፍጥረታትን ፈጠረ። በምሳር የሚቆረጡ፣ በማጭድ የሚታጨዱ፣ በጥፍር የሚለቀሙ አዝርዕትን፣ አትክልትን ዕፀዋትን ፈጠረ።

እግዚአብሔርም ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬ የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል አለ፤ እንዲሁም ሆነ። ምድርም ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን እንደወገኑ ዘሩም ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን እንደወገኑ አበቀለች። ዘፍ 1፥11-13

ሣሩ ለከፍከፉ እንጨቱ ለደገፉ ባዕሙ፣ ልምላሜው መዓዛው ያማረ የተወደደ ሆኖ አንድ ጊዜ አብቦ አፍርቶ ተገኘ።

፪. ወርእየ እግዚአብሔር ከመ ሠናይ እንዳለ ሙሴ።ዘፍ ፩፥፲፪-፲፬

እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ። ዘፍ 1፥12-14

፫. ወተከለ እግዚአብሔር ገነተ እምመንገለ ምሥራቅ ልዕልተ እምድር ወታሕተ እምሰማይ። ዘፍ ፪፥፰-፱

www.ethiopianorthodox.org

፰. ወእምዝ ወረደ መንፈስ እግዚአብሔር ወቦአ ውስተ ገነት ወቀደሰ ኲለንታሃ ወኲሎ ዘውስቴታ ይእቲኒ አእመረቶ ወሰብሐቶ ለኬንያሃ::
ከዚህም በኋላ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ገነትን ሁለንተናዋን ቀባት፣ አነጻት፣ አከበራት እርሷም ፈጣሪዋን አወቀች አመሰገነች::

፱. ወእምዝ ወረደ መንፈስ እግዚአብሔር ወቦአ ውስተ ውቅያኖስ ወቀደሰ ኲለንታሃ ወኲሎ ዘውስቴታ ይእቲኒ አእመረቶ ወሰብሐቶ ለኬንያሃ::
ከዚህም በኋላ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ውቅያኖስን ሁለንተናዋን ቀባት፣ አከበራት፣ አነጻት እርሷም ፈጣሪዋን አወቀች አመሰገነች::

፲. ወእምዝ ወረደ መንፈስ እግዚአብሔር ወቦአ ውስተ ዛቲ ዓለም ወቀደሰ ኲለንታሃ ወኲሎ ዘውስቴታ ይእቲኒ አእመረቶ ወሰብሐቶ ለኬንያሃ::
ከዚህም በኋላ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ይህችን ዓለም ሁለንተናዋን ቀባት፣ አከበራት፣ አነጻት እርሷም ፈጣሪዋን አወቀች አመሰገነች::

፲፩.ወእምዝ ወረደ መንፈስ እግዚአብሔር ወቦአ ውስተ ነፋስ ወቀደሰ ኲለንታሃ ወኲሎ ዘውስቴታ ይእቲኒ አእመረቶ ወሰብሐቶ ለኬንያሃ::
ከዚህም በኋላ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ነፋስን ገብቶ እንደ ምግባሯ ለይቶ ቀባት፣ አከበራት፣ አነጻት እርሷም ፈጣሪዋን አወቀች አመሰገነች::

www.ethiopianorthodox.org



፲፪.ወእምዝ ወረደ መንፈስ እግዚአብሔር ወቦአ ውስተ ገሃነመ እሳት ወቀደሰ ኲለንታሃ ወኲሎ ዘውስቴታ ይእቲኒ አእመረቶ ወሰብሐቶ ለኬንያሃ::
ከዚህም በኋላ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ገሃነመ እሳትን ሁለንተናዋን ቀባት፣ አከበራት፣ አነጻት ከትኩሳት ላይ ትኩሳት ጨመረላት እርሷም ፈጣሪዋን አወቀች አመሰገነች::

፲፫.ወእምዝ ወረደ መንፈስ እግዚአብሔር ወቦአ ውስተ በርባሮስ ጽልመት ወቀደሰ ኲለንታሃ ወኲሎ ዘውስቴታ ይእቲኒ አእመረቶ ወሰብሐቶ ለኬንያሃ::
ከዚህም በኋላ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ በርባሮስን ሁለንተናዋን ቀባት በጽልመት ላይ ጽልመት በፅናት ላይ ፅናት ጨመረላት እርሷም ፈጣሪዋን አወቀች አመሰገነች::

፲፬.ወእምዝ ዓርገ መንፈስ እግዚአብሔር ውስተ አርያም እም ውስተ ቀላየ ፅልመት ኅጻጉጽ ፍኖታ በከመ ውእቱ አእመረ::
ከዚህም በኋላ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ በርባሮስን ቀብቶ እርሱ ባወቀው መንገድ ወደ አርያም ዓረገ::

፲፭.ነዋ ተፈፀመ ተፈጥሮ ዓለማት::
እነሆ የዓለመ እሳት፣ የዓለመ ነፋስ፣ የዓለመ መሬት፣ የዓለመ ማይ ተፈጥሮ ተፈፀመ::

እኛ እግዚአብሔርን ወጣ ወረደ ማለታችን በዘፈቀደ /እርሱ በፈቀደ/ መታየቱን መናገራችን ነው እንጂ እግዚአብሔርስ መውጣት መውረድ የለበትም::

አኪምን ወለደ፣ አኪምም ኤልዩድን ወለደ፣ ኤልዩድም
አልዓዛርን ወለደ። ማቴ 1፥12-16

፲፮.ወአልዓዛር ወለዶ ለቅስራ፣ ወቅስራ ወለዶ ለኢያቄም፣
ወኢያቄም ወለዳ ለእግዚእትነ ማርያም፣ ወእግዝእትነ
ማርያም ወለደቶ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘክሮቱ
ይደሉ ሰጊድ።

አልዓዛርም ቅስራን ወለደ፣ ቅስራም ኢያቄምን ወለደ፣
ኢያቄምም እግዝእትነ ማርያምን ወለደ፣ እግዝእትነ
ማርያምም ክብር ምስጋና ይገባውና ጌታችንን ኢየሱስ
ክርስቶስን ወለደችው።

፲፮.ወአልዓዛር ወለዶ ለማታን ወማታን ወለዶ ለያዕቆብ፣
ወያዕቆብ ወለዶ ለዮሴፍ ዘውእቱ ፈኃሪሃ ለእግዝእትነ
ማርያም፣ ወዮሴፍ ወለዶ ለያዕቆብ ኤጲስ ቆጶስ
ዘኢየሩሳሌም። ማቴ ፩፥፲፮-፲፯

ዳግመኛም ትውልድ አልዓዛርም ማታንን ወለደ፣ ማታንም
ያዕቆብን ወለደ፣ ያዕቆብም ዮሴፍን ወለደ ዮሴፍም
የእግዝእትነ ማርያም ጠባቂዋ ሞግዚቷ ነው።ማቴ 1፥16-17
ይኸውም ዮሴፍ የኢየሩሳሌምን ኤጲስ ቆጶስ ማር ያዕቆብን
ወለደ።

፲፯.ወእስከዝ ኮነ ትውልድ ፷ወ፮ ወዘመን ኮነ ፶፻ወ፭፻።
እስከዚህ ድረስ ትውልዱ ስድሳ ስድስት ነው። ዘመኑም
አምስት ሺህ አምስት መቶ ነው።
እስከዚህ ያለው ዓመት ፍዳ ዓመተ ኩነኔ ይባላል።




www.ethiopianorthodox.org

አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ግን በገጽ ፪፻፷
ቁጥር ፲፫ ላይ እንደተጠ ቀሰው ጌታችን መድኃኒታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ ለአዳም በገባለት ቃል ኪዳን መሠረት
ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከልጅ ልጅህ ከተባለችው ከድንግል
ማርያም ተወልዶ በመስክ ላይ ድሆ በቀራንዮ አደባባይ
በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ
ለባሕርይ አባቱ ክሶ ከዲያብሎስ አገዛዝ ነፃ አደረገው፤
ከሲኦል አወጣው ገነትም አስገባው፤ የሰጠውም ተስፋ በዚህ
ተፈጸመ። በዚህም ምክንያት ከዚህ በኋላ ያለው ዘመን
ዓመተ ሥጋዌ፣ ዓመተ ምሕረት ተባለ።

፲፱.ተፈጸመ ሥነ ፍጥረት መጽሐፈ ቅዱስ ኢጲፋንዮስ ዳግማይ
ሙሴ እስመ ፈከረ ዳግማየ ኦሪተ ዘውእቱ አክሲማሮስ።

ሁለተኛ ኦሪትን የተረጐመ ይህውም የሁለተኛው ሙሴ
የቅዱስ ኤጲፋንዮስ የሥነ ፍጥረት መጽሐፈ አክሲማሮስ
ተፈፀመ።

እስከዚህ ድረስ የዕለተ ዓርብ ሥነ ፍጥረት ነው። ዓርብ
ማለት ስድስት ዕለት ማለት ነው። ዓርብ ለፍጥረት ስድስተኛ
ለቀመር አራተኛ ለፀሐይ ሦስተኛ ማለት ነው። ስድስት
ዕለት ሀያ ሁለት ሥነ ፍጥረት ይህ ነው። ይህስ የተፈጸ
መው በምን ቀን ነው ቢባል ሚያዝያ አራት ቀን ነው።

www.ethiopianorthodox.org

የስድስት ቀን ሥነ ፍጥረት ከብዙ ብጥቂቱ ከሙሉ በከፊል ደረሰ ተፈጸመ።

እንግሥቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን የፍጥረታት ፈጣሪ ክብር ምስጋና ይድረሰው አሜን።

ሬታና ቤተክር
ቤተ መጻሕፍት
መ.ገ.ጊ.

www.ethiopianorthodox.org